# የመለስ አምልኮን በጨረፍታ(ክፍል ሦስት)
## የዜሮ ድምሩ ስብስብ ውታፎች

ዮናስ 7/13/12

ምርጫ 97 ካለፈ እነሆ ሰባተኛ ዓመቱን ደፍኖ ወደስምንተኛው እየተሸጋገረ ነው ። ሆኖም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲወሳ ፣ ስለዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሲነሳ፣ ስለልማትና ስለህግ የበላይነት ሲተረክ ልክ እንደ ያ ትወልድ ታሪክ፣ ልክ እንደአፄዎቹ ዘመን ትዝታ ምርጫ 97ም አብሮ መነሳቱ  እንደቀጠለ ነው።

ከምርጫ 97 ትውስታዎች ብዙ ጊዜ የነገር ማጣፈጫም ሆነ የምርጫ
ፖለቲካ ሆኖ የሚነሳው ደግሞ ሚያዚያ 30ና የቅንጅቱ ሰልፍ ነው ።ከምርጫ 97እና ድህረ ምርጫውን ተከትሎ የነበሩ ክስተቶችን በተመለከተ በወቅቱ ተዋናዮች የተፃፉ መፃህፍትን ሁሉ ስንፈትሽ ሚያዚያ 30 የነበረው የቅንጅቱ ሰልፍ ያልተጠቀሰበትን እምብዛም አናገኝም።  ´|የመለስ አምልኮ´ የተባለው የመጣጥፍ ጥርቅም 3ኛ ክፍል ታላላቅ ሃገራዊ ክስተቶች የሚል አብይ ርዕስ የያዘና የመጀመሪያውን አጀንዳም እዚሁ ሚያዚያ 30 ላይ ያደረገ "ትዝታ ሚያዚያ 30" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው።

የመጣጥፉ ጭብጥ ከዓድዋ የድል በዓል በመቀጠል በኢትዮጵያ ብሄራዊ በዓል ሆኖ መከበር ያለበት ሚያዚያ 30 እንጂ ግንቦት 20 መሆን አልነበረበትም የሚልና ይህንኑ ለማጠናከረም የደርጉን አብዮታዊ በዓልና የንጉሱን  ሲመት በአልም የመንግስት በዓል እንጂ ብሄራዊ በዓላት መሆን አልነበረባቸውም በሚል የቀረበ መጣጥፍ ነው።

በወቅቱ ቅንጅቱ |አልተሸነፍኩም´ "ምርጫውም ተጨብርብሯል "ሲል እንደመከራከሪያ ምክንያት ያቀርብ የነበረው በሚያዚያ 30 ሰልፍ ላይ የተገኘውን ህዝብ  መሆኑን እናስታውሳለን።

ገዢው ፓርቲ ደግሞ በአንፃሩ በርካታ ደጋፊዎች በሰልፉ ላይ መገኘታቸውን ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ መሸነፉን በማመን የአዲስ አበባ ነዋሪ 85 ከመቶ የሚሆነውን የገጠር ነዋሪና የአብዛኞቹን የክልል ከተሞች አይወክልም። አንድ ሰው የሚኖረው የመምረጥ መብት አንዴና አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን ይኸውም በተመዘገበበት የምርጫ ክልልና ነዋሪ በሆነበት ቀበሌ ብቻ ነው። ያም ሆኖ ግን በአዲስ አበባ በቅንጅቱ ሰልፍ ላይ የተገኘው ሁሉ የምርጫ ካርድ አለው ማለት አይቻልም፣ወዘተ የሚሉ ሃሳቦችን ሲሰነዝር እንደነበርም እናስታውሳለን።

ቅንጅቱና ደጋፊዎቹ የገዢውን ፓርቲ ትንታኔ በወቅቱ ባይቀበሉትም ከጊዜ በኋላ ለንባብ የበቁትን የወቅቱን ፖለቲካ የተመለከቱ መፃህፍቶችና መጣጥፎች ግን የገዢውን ፓርቲ ትንታኔ ትክክል እንደነበር የሚያመላክቱ ሆነው አግኝቼአቸዋለሁ።

ይህን ጉዳይ ከሚያረጋግጡት መጣጥፎች መካከልም "ትዝታ ሚያዚያ 30" የሚለው የተመስገን መጣፍ ነው ።

በሰኔ 29/2004 የፍትህ ጋዜጣ እትም ላይ ተመስገን በወቅቱ የየትኛውም ፓርቲ አባልና ደጋፊ እንዳልነበር በማውሳት ከብርቱካን ሚደቅሳ ጋር በጓደኛው አማካኝነት መተዋወቁን እንደገለፀልን በሁለተኛው የመለስ አምልኮን ጨረፍታዬ መጥቀሴን አንባቢዎቹ አስታውሱልኝ፡፡

በመቀጠል ወደመለስ አምልኮ |ትዝታ ሚያዚያ 30´ ስንመጣ |እኔም ብሆን ለስምንት ሰዓት ዝግጅት ወደ አደባባዩ የሄድኩት ገና ከማለዳው ሁለት ሰዓት ተኩል ነው´ ገጽ 120 |---- እንደእኔ የየትኛውም ፓርቲ ተከታይ ያልሆኑ ነገር ግን መደገፍም መቃወምም ስልጣን የያዘ ፓርቲ የሚሰጠውና የሚነሳው መብት አለመሆኑን ለማሳየት አደባባይ የደረሱ ብዙዎች ናቸው"ገጽ 121

ስለሆነም ያ ሁሉ ሰልፈኛ መራጭ እንዳልነበር ገዢው ፓርቲ ያቀረበው መከራከሪያ ትክክል ነው ማለት እንችላለን ።ይህ ብቻ አይደለም ከቅንጅቱ መሰባበር በኋላ አብዛኛውን የቅንጅት ደጋፊና አባላቱን ይዞ በአዲስ መልክ የተመሰረተው ደግሞ አንድነት መሆኑን እናውቃለን ።

"በጨዋነት እየተካሄደ ያለው ገዢው ፓርቲን የመቃወም እና ቅንጅቱን የመደገፍ ሁኔታ አሁንም በጨዋነት ቀጥሏል።" አሁን ደግሞ ከጨዋነት በማፈንገጥ በአመጽና በአመጽ ቅስቀሳ በፍትህ ጋዜጣ በኩል የቅንጅቱ ስብርባሪ የሆነውን አንድነት መደገፍና ገዢውን ፓርቲ መቃወም ቀጥሏል።

ከዚህ በመነሳት ተመስገን ነፃ ጋዜጠኛ ሳይሆን የአንድነት ደጋፊ ወይም  የቅንጅት ስብርባሪ ነው ማለት ይቻለናል።

ሚያዚያ 30 ብሄራዊ በዓል ሊሆን ያልቻለበትና የማይችልበት   (ተመስገን ሊጽፈው ባይፈቅድም) በርካታ ምክንያቶች አሉ። ግንቦት 20 ብሄራዊ በዓል ከሆነባቸው አጅግ በርካታ ምክንያቶች ውስጥ ግን ጥቂቶቹን እኔ አናገራለሁ።

ግንቦት 20 ለዘመናት ጥያቄ ሆኖ የዘለቀው የብሄር ብሄረሰቦች መብት  ምላሽ ያገኘበት፣ ከጭቆና ወደልማት የተደረገው ፍልሚያ በድል  የተጠናቀቀበት ፣ መላው ብሄር ብሄረሰቦች ፈቅደውና አምነው ይህን ተመስገን እና መሰሎቹ እንዳሻቸው ለመፈንጨት ያስቻላቸውን ህገመንግስታዊ ስርዓት ለማበጀት የበቁበት ፣ የልማት ባለቤት እና ቀጥተኛ ተጠቃሚ  መሆን የቻልንበት፣

የሃይማኖት እኩልነት በይፋ የታወጀበት  ወዘተ እለት ነው ግንቦት 20። ስለሆነም ግንቦት 20 የታጋዮች ቀን ሳይሆን የኢትዮጲያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በመሆኑ ብሄራዊ በዓል መሆን የሚበዛበት አይደለም።

ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ በኢትዮጵያ የህክምና ሳይንስ ታሪክ ውስጥ ከፍ ያለና የጎላ አሻራ ያላቸው ብርቱ ምሁርና ቀላል የማይባል የፖለቲካ ስብእና የነበራቸው መሆኑን እናውቃለን። ታዲያማ "የፕሮፌሰር  አስራት ወይስ የመኢአድ ሙት አመት" የሚለው የተመስገን መጣጥፍ የፕሮፌሰሩን በቅዱስ ባለወልድ  የመቃብር ስፍራ ማረፍ ለምን? ሲል የሚጠይቅና ሙታን የሚያናግር መንፈስ አይነት ዝንባሌ ያለው መጣጥፍ  ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ እና ስልጣኔ እንዲሁም ሌሎች ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ውለታ የሰሩ ግለሰቦች በሞቱ ጊዜ ካቴድራል ስላሴ  ማረፊያቸው እንደሆነ የሚያወሳው ተመስገን የፕሮፌሰር አስራትን ግብአተ መሬት አፈጻጸም ትክክል አይደለም ሲል  በሽሙጥ መልኩ ለመሞገት ይሞክራል። የኢትዮጲያ ባለውለታ የነበሩት ፕሮፌሰር ለምን ስላሴ አልተቀበሩም? ሲል የሚጠይቀው ተመስገን ጋዜጠኛ ከሆነ ወይ የፕሮፌሰሩን ቤተሰቦች ወይም ሌላ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ ምክንያቱን ማወቅና ማሳወቅ ስራው ነበር።

ሆኖም አጀንዳው ጥላቻ ስለሆነ የፕሮፌሰሩን በስላሴ ያለመቀበር ወደ ገዢው ፓርቲ ይሁንታና ክልከላ ለማላከክ ወይም ለማያያዝ እገሌ እከሊት እያለ በስላሴ መካነ መቃብር ያረፉ ባለውለታዎቻችንን ይገልጽና "ሌላው ቀርቶ የደህንነት ሚኒስትር የነበሩት ክንፈ ገብረመድህን፣ ፕሮፌሰር ክንፈ አብረሃ ፣ እያሱ በርሄ ---- በስላሴ መካነ መቃብር ስፍራ የመቀበር ዕደል አግኝተዋል።" ገጽ 124 ሰረዝ የኔ ።

ሌላው ቀርቶ የምትለው አማረኛ ምን ማለት ነች? ብለን ጥያቄ ካነሳን በተመስገን አገላለጽ መካነ መቃብሩ ለነክንፈ አይገባቸውም ማለት ነው። እከሌ እና እከሊት ተብለው ከላይ የተዘረዘሩት  እና ፕሮፌሰር አስራት ይገባቸዋል      ለማለት ነው። ይህ ተራ የጥላቻ ፖለቲካ ቢሆን እንጂ ለኢትዮጲያውያን ምንም ጠብ የሚል ነገር የሚያመጣ የነፃነት ተጋድሎ አይደለም።

"ባራክ ኦባማ ስራ ይባዛባቸዋል። መለስ ዜናዊ ስብሰባ ይበዛባቸዋል። ስብሰባ፣ ስብሰባ፣ ስብሰባ ------ ቀጥሎ ደግሞ ግምገማ፣ ግምገማ፣ ግምገማ ---"  "ሰኞን ከመለሰ ዜናዊ ጋር" የሚል ርዕስ ከተሰጠው መጣጥፍ የተወሰደ ነው። ይህ መጣጥፍ መሰረት ያደረገው ክቡር ጠቅላይ ሚኒሰትሩ ከአርቲስቶች ጋር ያደረጉትን ውይይት ቢሆንም በየደረጃው ከሚገኙ የወጣት፣ የሴትና ሌሎች ማህበራት ጋር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያደረጓቸውን ውይይቶች የሚያጣጥል ነው።

በኢህአዴግ መዋቅር ውስጥ ያሉ አደረጃጀቶችን እና የግምገማ ስርዓቱን በተደጋጋሚ የሚኖቁሩት የዜሮ ድምሩ ስብስቦች የግምገማን ጥቅም እና ያለግምገማ የትም መድረስ እንደማይቻል ሳይረዱት ቀርተው ሳይሆን ስላልሆነላቸው ብቻ ነው። ታዲያማ" ባለራዕይ ነፃ የወጣቶች ማህበር" ፣ "የአንድነት የወጣቶች ፎረም "የሚሉና መሰል  ሳይጸነሱ የሚጨነግፉ አደረጃጀቶችን ለምን ለማቋቋም ጥረት አደረጉ? የነሱ ያልተሳካ እንደሆን አደረጃጀትን ከመሰረታዊ የፓርቲ እና ፖለቲካዊ መርሆ ውጪ ማድረግ  እንዴትስ ይቻላል?

በአንድነት ፓርቲ ውስጥ  መደራጀት ቢኖር፣ ግምገማና ስብሰባ የተጠናከረ ቢሆን መች የመርህ ይከበር የሚልና የአሁኑ ቡድን  ይፈለፈሉ ነበር። ቅንጅቱ የተፈረካከሰው፣ አንድነቱ የተበታተነው መድረኩ መዋሃድ ተስኖት ዛሬም ድረስ በነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ የሞት ትንቅንቅ ላይ የሚገኘው ከግምገማ እጦት እና ከአደረጃጀት ፍልስፍና ውጪ የሆነ የጥላቻ፤የአምባገነናዊ አስተሳሰብ በመንሰራፋቱና የሽኩቻ ፖለቲካዊ መዋቅር በመዘርጋቱ ምክንያት እንደሆነ እንኳን ሌላው ዜጋ እነርሱም ቢሆኑ ያውቁታል ብዬ አምናለሁ፡፡
በርግጥ ግምገማ በአሰራር መርህ ስለተቀመጠ ብቻ የሚደረግ  እንዳይደለ ሁሉ አደረጃጀትም በግዳጅ የሚሆን አይደለም። ፖለቲካዊ ጥበብንና ብልሃትን እንዲሁም ህዝባዊነትንና የዓላማ ጽናትን የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው።

በነገራችን ላይ የባለራዕይ ወጣቶች ማህበርን ከአንድነት ፓርቲ ጋር ያያዝኩ ከሀምሌ 3/2004 የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ በቂ ማስረጃ በማግኘቴ ነው። የማህበሩ ሰብሳቢና መስራች ሃብታሙ አያሌው ከዚህ ቀደም በፍትህ ጋዜጣ ላይ ስለ ነፃ ማህበራትና መሰል አጀንዳዎች ብዙ ቢለፍፍም በፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ መጣጥፌ ሃብታሙ የዜሮ ደምሩ ስብስብ የዕብደት ጎዳና መገለጫ አንደሆነ አሳይቼ ነበር።

የአዲስ አበባ ወጣቶች ፎረም ፕሬዚዳንት የነበረው ሃብታሙ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የህዘብ ግንኙነት ሃላፊም ሆኖ የሰራና ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የዘመረ ወጣት እንደነበር በዚሁ መጣጥፌ ገልጬ ነበር። እሱም በየዲስኩሮቹ አናት ላይ ቀድሞ የነበረበትን ሁኔታ እና አብዮታዊ ዴሞክራት እንደነበር  አረጋግጧል።

ለጥገኛ ፍላጎቱ የማርያም መንገድ እንኳ ከከለከለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር በመላተሙና የግምገማ ሰለባ በመሆኑ  የተሰናበተው ሃብታሙ "ነፃ መሆን ስለፈለግሁ  ነው ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር የተፋታሁት" ይለናል ።

የአዲሰ አበባ ወጣቶች ፎረም ነፃ ካልነበረ መልቀቅ የነበረበት መቼም የፎረሙ ፕሬዚዳንት ሆኖ በነበረበት ወቅት አለያም ቀደም ብሎ መሆን ይገባው ነበር። ዕውነታው ግን ሃብታሙ ከወጣች ፎረም ፕሬዝዳንትነቱ በኋላ የነፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ  እና የካቢኔ አባል

ሆኖ ሰርቷል፡፡ ታድያስ በካቢኔ ደረጃ ከልማት ጎዳና በማንፈገጡ እና ሳይበስል መጨንገፉ በግምገማ በመረጋገጡ ለመልቀቅ የተገደደው ሃብታሙ የዜሮ ድምር አስተሳሰብ እንዲህ ነውና ቀድሞ ስለለቀቀው የወጣቶች ፎረም ነፃ ካለመሆን ጋር አጀንዳውን ለማያያዝ ሞከረ፡፡ ሞከረናም አልቀረም የዜሮ ድምር ስደተኞቹን የሚሰበስቡት ፍኖተ ነፃነትና ፍትህ ጉያ ስር ተወተፈ። ተወትፎም ሲያበቃ "ነጻ" ማህበር ነው በሚለው የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ስም አብዮታዊ ዴሞክራሲን ማውገዙን ተያያዘው፡፡

በርግጥ የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ነፃ ከሆነ ስራው የነፃ ማህበራት መርሆዎችን ተከትሎ የወጣቱን ፍላጎት ማሳካት ነው ያለበት ?ወይስ አብዮታዊ ዴሞክራሲን በመኮነን የተቃውሞውን ጎራ ቀልብ መሳብና በዚህም በተገኘ ውጤት ልክ እንደሰሞኑ ከዶክተር ሃይሉ አርአያ ጋር የአንድነት አባላትን መድረክ መምራት?። ይህ ነው እንግዲህ የጎራው መደበላለቅና የጋሪ ፈረስ ጉዞ ውልል ብሎ የሚታየን። በአንድነት ቤት ስብሰባና ግምገማ ስለሌለም "ይህ ነፃ ማህበር አይደለም እንዴ?፣ ታድያ ነጻ ከሆነ ከኛ ጋር ምን ያደርጋል" ብሎ የሚጠይቅ የለም፡፡ ስለሃብታሙና የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር በስፋት የምመለስበት መሆኑን በማስመር ወደ ነበርኩበት አጀንዳ ልመለስ÷

“ኢህአዴግ ምን ያድርግህ” ይላል ሌላኛው የተመስገን መጣጥፍ። በዚህ መጣጥፍ ላይ ተመስገን ለማሳየት የሞከረው በኬንያ ያደረገውን የሥራ ቆይታ በመንተራስ በኬንያ ያለውን የዴሞክራሲና የልማት ሂደት ከኢትዮጵያ አንጻር መፈተሽ ነው፡፡

በዚህ ፍተሻውም ኬንያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ ከኢትዮጵያ የተሻለ ዕድል ያላትና የቀረበች መሆኑን ሲናገር የኬንያን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት፤ የኬንያን ነፃ የገበያ ሥርዓት፣ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ገበያውን በማሳያነት ያቀርባል፤ ኬንያ የአፍሪካ የዴሞክራሲያዊ ሀገር ተምሳሌት ነች ሲል ለሙግቱ ማሳያነት የሚያቀርበው ደግሞ የነፃ ጋዜጦችን መበራከትና የአለም አቀፍ ተቋማት በብዛት በኬንያ የመኖራቸውን ጉዳይ ነው፡፡

ነገር ግን ወደ መሰረት ልማት ሲመጣ አዲስ አበባ በምን ጣዕሟ ይለንና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገለጫ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ ግንባር ቀደም ስለሆኑት ተቋማትና ስርዓቱ ሲያወሳ ግን ለኬንያ ያቀረበው መወድስ ወደ ሙሾ ይለወጥበታል፡፡ በዚህም መጣጥፉ ከኬንያ እንድንማር ሳይሆን የኢትዮጵያን መንግስት እና ስርዓት በተገኘው አጋጣሚ ለመምታት እንደተለመደው የቀረበ መጣጥፍ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ አንዳንድ ማሳያዎች ከዚሁ መጣጥፍ ላይ እንምዘዝ

“ሚዚ ሚዚ (ሌባ ሌባ) ብለህ ከጮህክ እና ሌባ ያልከውን ሰው ከያዝከው መንገደኛው ሁሉ ተባብሮ እላዩ ላይ ጎማ አጥልቆ በእሳት ይለኩሰዋል፡፡ አልያም በድንጋይ አናቱን ፈልጠህ (ገለህ) በኩራት መሄድ በናይሮቢ የተለመደ ነው ።"ገጽ 154 ሠረዝ የኔ፡፡

ገለህ በኩራት የምትሄድበት ሀገር እንዴት ሆኖ ነው የዴሞክራሲና የነፃነት መገለጫ ሀገር ሆኖ የሚቀርበው ብለን ጥያቄ እንደምናነሳ የገመተው “ነፃው” ጋዜጠኛ የሞኛ ሞኝ ብልጠቱን በመጠቀም ከነፃ ፕሬስም በላይ የህግ የበላይነት መገለጫ የሆኑትን  ዋነኛ ጉዳዮች ሁሉ የባህል ጉዳዮች አድርጎ በማቅረብ ሊያጃጅለን ይሞክራል፡፡

“ሆኖም የመንግስትን አስተዋጽኦ በማይጠይቁ እንደባህል ባሉ ነገሮች አትጠራጠር ኢትዮጵያውያን ከኬንያውያን ሺህ ክንድ ያስከነዳሉ፡፡” ገፅ 154 ሠረዝ የኔ፡፡ ሰው ተገድሎ በኩራት መሄድ ለተመስገን የፀጥታና የህግ የበላይነት ጉዳይ ሳይሆን እንደባህል ያለ ነገርና የመንግስትን አስተዋጽኦ የማይጠይቅ ተራ ጉዳይ ነው፡፡የጋዜጣ ብዛትና የአለም አቀፍ ተቋማት መበራከት ደግሞ የህግ የበላይነት ጉዳይ ነው፡፡

ሌላ ማሳያም ልስጣችሁ፡ “ በናይሮቢ ጥቂት ሽልንጎችን እንኳ በአደባባይ ይዞ መውጣት መሳሪያ የታጠቁ ዘራፊዎችን ሊያመጣብህ ይችላል፡፡ዘራፊዎቹም መሳሪያቸውን ከደቀኑብህ ህይወትህ ይተርፍ ዘንድ የሚያዙህ ሶስት ነገሮች አሉ፡፡  ሶስቱንም የግድ መፈፀም አለብህ፡፡ “ ዞረህ እንዳታይ”፣ “ተኛ" እና “ያለህን በሙሉ ዘርግፈው”፡፡ ከሶስት አንዱን ጥሰህ ዞረህ ብታይ ወይ ባትተኛ ወይ ያለህን ባትዘረግፍ ለህሊና ፀሎትም ፋታ አታገኝም፡፡ በፍጥነት በጥይት አናትህን በርቅሰውታል፡፡ በኬንያ የፀጥታ ሰራተኞችም እንዲሁ ከፓርላማው የተሰጣቸው ስልጣን አለ፡፡ በፖሊስ ተመዝግበው የሚፈለጉ ሌቦችን ሲያገኙ “እጃቸውን ቢሰጧችሁ እንኳ ወደ ጣቢያ እንዳታመጧቸው” የሚል ትዕዛዝ ግልጽ ነው፡፡ እንዳገኘህ አንበርክከህ በጥይት በላቸው ነው የተላለፈው መመሪያ፡፡ ይሄም የናይሮቢን ኑሮ በስጋት የተሞላ አድርጎታል፡፡” ገጽ 154

እርሱ እንደሚለው ግደል ብሎ መመሪያ የሚያስተላልፍ ፓርላማ፣የተሰጠውን ትዕዛዝ ለምን?ብሎ የማይጠይቅ እና  የዜጎቹን አናት በጠራራ ፀሃይ  የሚበረቅስ የፖሊስ መዋቅር፤ በስጋት የተሞላ ኑሮ ያለባት ከተማ እንዴትስ ሆና ነው ታድያ የዴሞክራሲና የስኬት መገለጫ በማድረግና  ኢትዮጵያን አሳንሶ  በማዬት ለንጽጽር ማቅረብ የሚቻለው? ለነገሩ የኬንያን ጉዳይ ለራሳቸው ለኬንያውያን እንተውላቸውና ወደ ርዕሰ ጉዳያችን እንመለስ፡፡

እውነት ዴሞክራሲ ማለት በስጋት እየኖሩ ጋዜጣ ማንበብ ነው?። በፍርሃት እየኖሩ ሬድዮ ማዳመጥ ነው?፡፡ ነፃ ገበያውስ እየተዘረፉና እየተገደሉ በእድልና በአጋጣሚ የሚደረግ ግብይት ነው?፡፡ እናንተው ፍረዱ፡፡ “ለእነሱ መንግስትም ሆነ የመከላከያ እና የፖሊስ ሰራዊት አልያም የደህንነት ሰራተኞች የህዝብ አገልጋይ እንጂ በህዝብ ተጧሪ እና ተገልጋይ አይደሉም፡፡ ከጋዜጦቹ ጋርም 7ቱ የግል ቴሌቭዥን ጣቢያዎች ዋነኛ የህዝብ አይንና ጆሮ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው በኬንያ ጋዜጠኛ የሚንስትርን ያህል ተሰሚ እና ተከባሪ የሆነው” ገጽ 148 ይላል ሌላው ማሳያዬ

ታድያ መንግስትና የመከላከያ እንዲሁም ፖሊስ የህዝብ አይንና ጆሮ ከሆኑ ጥቂት ሽልንጎችን ያየዙ ግለሰቦች  በጠራራ ፀሐይ ለምን ይገደላሉ? ጋዜጦቹስ የህዝብ አይንና ጆሮ ከሆኑ ይህን ሥርዓተ አልበኝነት መታገል ለምን ተሳናቸው? ተመስገን አጀንዳውና ዓላማው ሌላ ስለሆነ ተምታቶበት የተምታታ ትረካውን ይቀጥላል፡፡

"የአፍሪካ ህብረት መቀመጫነትን ክብር ሳይቀር ታቅፈን በርካታ አለም አቀፍ ድርጅቶች ግን የአፍሪካ ዋና ቢሮአቸውን ናይሮቢ ላይ ነው ያደረጉት፡፡. . . . ይሄ ለምን የሆነ ይመስልሃል? ጠንቋይ አትጠይቅ መልሱ ቀላል ነውና፡፡ ኢትዮጵያ ሀገርህ በአምባገነን ስርዓት ስስለምትተዳደር ለእነዚህ ታላላቅ ኩባንያዎች ዋስትና መስጠት ስለማትችል ነው፡፡  <u>በአናቱም</u> መንግስትህ የህግ የበላይነት፣ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብት ይከበር ለሚሉ ተቆርቋሪዎች በጎ ፊት ስለሌለውም ነው" ገጽ 148

መጀመሪያ ከባድ የሆኑ ነገሮችን ለማወቅ መፈለግና መመርመር እንጂ ጠንቋይ ቤት መሄድ ያለአዋቂዎች ተግባር ነው፡፡ ለተለያዩ ዓለምአቀፍ ወይም አህጉራዊ ድርጅቶች መቀመጫ የሚሆን ሃገርና ከተማ መረጣ የራሱ የሆነ በርካታ መስፈርቶችና ለሥራ አመችነት ጅኦግራፊዊ ስርጭት ያለው በመሆኑ በዚህ ላይ የተያዙ ሰነዶችን ማገላበጥ ይኖርብሃል፡፡ ለነገሩ አዲስ አበባ የበርካታ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችና በተለይም የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች መቀመጫ ከሆኑ ግምባር ቀደም ሃገራት መካከል አንዷ እንደሆነች ያውም  (ከኒዎርክና ጀኔቭ) ቀጥላ በሦስተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ አታውቅ ይሆን? ፈጥኖ ለማወቅና ለመለወጥ ፈቃደኝነቱና ጥረቱ እሰካለ ድረስ አለማወቅ በራሱ ብቻ ችግር አይደለምና ይህን በዚህ እንለፈው፡፡

በጠራራ ፀሐይ  ሰው እንደሚገደል የነገርከን፤ ሽልንግ የያዘ በጠራራ ፀሐይ ተንበርከክ፣ ተኛ፣ ያለህን ዘርግፍ የሚባልበት ሀገር እንዴትስ ሆኖ ነው የሰብአዊ መብት መከበር መገለጫ ሊሆን የሚቻለው? በአዲስ አበባ በቀይ ሽብር ዘመን ካልሆነ በስተቀር የቱ ጋር ነው በጠራራ ፀሓይ በየጎዳናው ላይ ሰው ሲገደል ያየሽው፣ እውነትም "ኢህአዴግ ምን ያርግህ፡፡" እኔም እልሃለሁ ኢህአዴግ ምን ያርግህ? በሶስተኛው ክፍል ከቀረቡት መጣጥፎች መካከል" እስክንድር ነጋን ሳስበው ሳስበው" የሚለውንና "ጓደኞቼን መልሱልኝ" የሚሉትን ያላነሳኋቸው በክፍል አንድና ሁለት ጨረፍታዬ እንዲሁም በፍትህና ዓምደኞቹን በጨረፍታ መጣጥፌ በስፋት ያየኋቸውና  ያው ከፍርድ ቤት ውሳኔ በመቅደም የተነፋ የፀረ የህግ የበላይነቶች ፊሽካ በመሆናቸው ነው፡፡ በክፍል 4 ጨረፍታዬ እንገናኛለን፡፡